YMCA ETHIOPIA

actionaid



# ጾታዊ ጥቃትን ለማስቆም የቆረጡ ሴቶች

በ 2016 ዓ.ም ድጋሚ የታተመ

actionaid

# መግቢያ

ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገራችን ባስከተለዉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ምክንያት ትምህርት ቤቶች የተዘጉበት፣ የተለያዩ ተቋማት አገልግሎት መስጠት ያቆሙበት እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ የተቋረጡበት ጊዜ ነበር፡፡ አክሽን ኤይድ ኢትዩጵያ የሴቶችን ጥቃት ለመከላከል ለተመረጡ 10 ልጃገረድ ሴቶች እድሜያቸዉ ከ15 ዓመት እስከ 24 ዓመት ያሉትን ሴቶች ከኢትዩጵያ ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር ጋር በመተባበር ስልጠና በመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ ሁለት ክፍለከተሞች ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 እና ወረዳ 04 እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 እና 10 ጥናት አድርጓል፡፡

ሴቶች በማህበረሰቡ ዉስጥ የተሰጣቸዉን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር እና ለዉጥ ለማምጣት ከእያንዳንዱ ግለሰብ ጀምሮ ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ትኩረት ሰጥተዉ በትብብር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተስፋፋበት ጊዜ በቤት ዉስጥ የሴቶች ጥቃት የጨመረበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን ልጃገረድ ሴቶች ስልጠና ከተሰጣቸዉ በኋላ በተመረጡ አባወራ ቤተሰቦች፣ የተለያዩ ተቋማት እንደ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማት፣ በመንግስት ተቋማት፣ በፖሊስ ጣቢያዎች እና የእምነት ተቋማት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ጥናቱን ያደረጉት ልጃገረድ ሴቶች ከጥናቱ በኋላ ያገኙትን ትምህርትና ልምድ ለማካፈል ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 እና ወረዳ 04 ወጣት ማዕከል እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ና ወረዳ 10 ወጣት ማዕከል እና ለኢትዩጵያ ወወክማ ወጣት ማዕከል ለልጃገረድ ሴቶች በጥናቱ ያገኙትን ልምድና ተሞክሮ እንዲሁም ያጋጠማቸዉን ችግሮችና ለገጠማቸዉ ችግሮች እንዴት መቋቋም እንደ ቻሉ ለወጣት ሴቶች ልምዳቸዉን ያካፈሉ ሲሆን ከጥናቱ በፊት፣ በጥናቱ ወቅት እና ከጥናቱ በኋላ ያላቸዉን ግንዛቤ፣ ለዉጥና የህይወት ተሞክሯቸዉን ለሌሎች ወጣት ሴቶች እና ለማህበረሰቡ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡



actionaid

"

ስሜ ኪዳን ፀሃይ አባይ ይባላል። ወደ ልጃገረድ ጥናት የገባሁት አክሽን ኤይድ ኢትዩጵያ በኢትዩ ጆብስ በኩል ባወጣው ማስታወቂያ አማካኛነት ነው፡፡ ለልጃገረድ ሴት ስልጠናው የተዘጋጀው ለ 3 ቀናት ሲሆን የስልጠናው ርዕስ ፣ ''ፓርቲሲፓቶሪ አክሽን ሪሰርቾ'' የሚል ነበር። ከጥናት፣ ትርጉምና አስፈላጊነት ጀምሮ፣ መረጃ እንዴት እንደሚሰበሰብ ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ ስልጠናው ግንዛቤ አስጨብጦናል፡፡ ልጃገረድ ሴቶች እርስ በርሳቸዉ እንዲተዋወቁ፣ እራሳቸውን መግለፅ እንዲችሉ አድርጓል - ስልጠናው፡፡ መረጃ የመሰብሰቢያ አማራጮችንም ወጣት ሴቶች ፣ እራሳቸው የመለየት ተግባር እንዲያከናውኑ ስልጠናው ረድቷል፡፡ በመቀጠልም ጥናት የሚደረግባቸው መንገዶች ተመረጡ፡፡

መረጃ ከማን እንሰብስብ ለሚለው ጥያቄ ልጆች ከእኩዮቻቸዉ ጀምረው በተመረጡ ክፍለ ከተሞች፣ ወረዳዎች ፣ በደረጃው ካሉ ስልጠናው ተሳታፊዎች ጋር ውይይቶች ተደርገው የመለየት ስራዎች ተከናወኑ፡፡ ጥናቱ የሚካሄድበትን መንገድ ከልጃገረድ ሴቶች ጋር በጋራ ወሰንን፡፡ ጥናቱ ምን ምን ጉዳዩች ላይ ያተኩር በሚል ከአክሽን ኤይድ ኢትዩጵያ ከቀረቡ 10 አማራጭ ሀሳቦች ውስጥ ሶስቱ በተሳታፊው ተመረጡ፡፡ ሪፖርት እንዴት ነው የሚደረገው፣ መረጃ የሚሰበሰብባቸው ወገኖች ጋር ስንደረስ እንዴት ነዉ የምናናግራቸው ፣ ከ መረጃ ሰጪዎቻችን ደህንነት ጋር በተገናኘና በሌሎች በተመረጡ ጉዳዩች ላይም ትኩረት ያደረገ ነበር የሶስቱ ቀን ስልጠና፡፡ ከስልጠናና ጥናቱ በኋላ ፣ በድህረ ጥናት ክፍለ ጊዜ በተመረጡ ልጃገረድ ሴቶች አማካኝነት ከስልጠናው በፊት ፣ ከስልጠናው በኋላ፣ በጥኛቱ ወቅት ፣ እንዲሁም ከጥናቱ በኋላ ባላቸው ግንዛቤ ላይ ዕዉቀት ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ውጤቱ አበረታች ነበር፡፡

በልጃገረዶቹ ላይ የሚገርም ለዉጥ አይቼባቸዋለሁ። ልጆች በመሆናቸው ከስልጠናዉ በፊት ብዙ ግንዛቤ አልነበራቸውም። ከጥናቱ በኋላ ግን በስልጠና ርዕሱ ላይ ያላቸው ግንዛቤና አመለካከት ተለውጧል።

"

“በጣም ጥሩ ለውጥ አምጥተዋል፡፡ በስለልጠናው ወቅት አንዳንድ ልጆች ራሳቸውን መግለፅና በድፍረት መናገር ይችሉ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ራሳቸውን መግለፅ አለመቻል፣ የመፍራትና በውይይት ወቅቶች ራሳቸዉን የሚገድቡ ነበሩ፡፡ ወደ ጥናቱ ከገቡ በኋላ ራሳቸዉን መለወጥ ችለዋል፡፡ በአጠቃላይ በሙሉ ሂደቱ ላይ ደስተኛ ነኝ፡፡ በጥናቱ ወቅት ያስተዋልናቸው ችግሮች ነበሩ፡፡ አንዳንድ የመረጃ ምንጨጫችን ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠት ተስተውሎባቸዋል፡፡ በተለይም በእድሜ ከፍ ያሉ የአካባቢ ነዋሪዎችና ትምህርት ቤት አካባቢ በሚገኙት ላይ ችግሩ ይጎላል፡፡ በእነዚህ ሰዎች ምትክ ሌሎች መላሾችን ተክተን ለመስራት ሞክረናል፡፡ አጥኚዎቹም በዚህ ተስፋ ቆርጠው ወደኋላ ሳይመለሱ ስራቸውን እንዲሰሩ ተደርጓል። ሌላው አንዳንድ የመንግስት ተቋማት ውስጥ አበል ክፍያ ከመፈለግ ጋር በተገናኘ ችግሮች ተከስተው ነበር፡ ለዚህም አማራጭ በማስቀመጥ ስራችንን መወጣት ችለናል። ልጃገረድ ሴቶች መረጃ ከሚሰጡን አካላት ጋር ጥሩ ተግባቦት በመፍጠር ፣ በተለይም ከወጣቶች ጋር ፣ መረጃውን መሰብሰብ ችለናል፡፡ከችግሩ ሰፋት አኳያ ብዙ መሰራት እንደሚያስፈልግ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ አክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር በዚህ ጉዳይ ዙሪያ መስራታቸው ለችግሮቹ መቀረፍ ተስፋ ሰጪ ነው፡፡

በተለይ የችግሩ ባለቤት የሆኑ ሴቶች ልጆችን ማሳተፉ፣ በልጅነት አዕምሯቸው ንቃተ ህሊናቸው እንዲጨምር ለማድረግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ጥሩ ጅማሮ ነው ብዬ አምናለሁ። ወጣቶቹ የጉዳዩ ባለቤቶች፣ ተጠቂዎቹ፣ እራሳቸው ድምፅ እንዲሆኑ ማድረግና እውቀታቸውና ንቃተ ህሊናቸው እንዲዳብር ማድረጉ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ አንዳንድ መረጃ ሰጪዎችንን ልጆች ከስነ-ተዋልዶ ጤና ጋር በተገናኘ ጥያቄ ስንጠይቃቸው ስለጉዳዩ ምንም ዓይነት መረጃ እንደሌላቸው ተረድተናል፡፡ ወጣቶች እራሳቸዉ በጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ ማደረጉ ችግሩን ከመሰረቱ ለመፍታት ትልቅ እድል ይፈጥራል፡፡ እንደዚህ አይነት ስራዎች በቀጣይ መሰራት ቢችሉ የሚል መልዕክት አለኝ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡”

ኪዳን ፀሃይ



“ነጃት ፋንታሁን እባላለሁ፡፡ 19 ዓመቴ ነው፡፡ የሁለተኛ ዓመት የአካውንቲንግ ተማሪ ነኝ፡፡ ወደ ልጃገረድ ጥናት የገባሁት በ ወወክማ አማካኝነት ሲሆን በልጃገረዶች ጥናት ላይ እንድሳተፍ ምክንያት የሆነኝ ጥናቱ በሴቶች ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ ነው፡፡ እኔም ወደፊት በዚሁ ማህበራዊ ዘርፍ ላይ መስራት ስለምሻም ነው፡፡ አቅጄ ነበር ተክባሮቼን የማከናውነው፡፡ ነገር ግን ከጥናቱ በኋላ በተሻለ መንገድ እንዳቅድ ረድቶኛል፡፡ በተጨማሪም እኔ የምኖረው፡፡ ጉርድ ሾላ አካባቢ ከቤተሰቦቼ ጋር ነው የምኖረው፡፡ ወንድሞች አሉኝ፡፡ ወንድሞቼ በሁሉም ነገር ያበረታቱኛል፡፡ የዚህ ጥናት ተሳታፊ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡፡ ወደፊት የተሻለ ስራ መስራት አስባለሁ፡፡ጥናት ከማካሄዳችን በፊት ምንም በሴቶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች ምንም አይነት ግንዛቤ አልነበረኝም፡፡ ጥቃት የደረሰባቸዉ ሴቶች ምን አይነት ህይወት እንደሚገፉ አላውቅም ነበር፡፡

ስለጥናቱ በአክሽንኤይድ ኢትዮጵያ ስልጠና ከተሰጠንና ወደ ጥናቱ ስገባ ጥቃት የደረሰባቸው ብዙ ሴቶች ታሪኮቻቸውን አጫወቱኝ፡፡ ለመንግስት አካላት ፣ ለጤና ጥበቃ ሰዎችና ህግ አስፈፃሚዎች የጥናቱን አስፈላጊነት አብራርተንላቸዋል፡፡ ከጥናቱ ያገኘነውን መረጃ መነሻ አድርገን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት፣ ከጤና አጠባበቅ ጤና ጣቢያ እና ፖሊስ ጋር የጥቃቱ ሰለባ ስለሆኑት ሴቶች ውይይት አድርገናል፡፡ ምን መደረግ እንዳለበትም መክረናል፡፡ ጥናቱን ስናካሄድ ከማህበረሰቡ ያጋጠሙን አንዳንድ ችግሮች ነበሩ፡፡ ከግንዛቤ ጉድለት አንዳንዶች ፍቃደኛ አልነበሩም፣ በራቸዉን ይዘጉ ነበረ፤ ጾታዊ ትንኮሳ ችግሮችም ደርሶብን ነበረ፡፡ በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙኝን ችግሮች ዙሪያ ከቤተሰቦቼ ጋር ግልፅ ውይይት አደርግ ነበር፡፡ ማህበረሰቡ ውስጥ ብዙ ችግሮች አሉ ችግሮቹን ለመቅረፍ መሰራት ያለባቸው ስራዎች አሉ፡፡ ስለዚህ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች መርዳት እንዳለብን ፣ ጥቃቶች እንዳይደርሱ ህብረተሰቡን ማስተማር፣ በትምህርት ቤቶች እና በእምነት ቋማት አካባቢ ግንዛቤ እና ስልጠና መሰጠት እንደሚገባ ተረድተናል፡፡ እኛም ጥቃት ለሚደርስባቸው ሴት እህቶች ድምፅ መሆን አለብን ፡፡”



## ነጃት ፋንታሁን





## ማርታ አጥላ

ማርታ አጥላ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ 20 ሲሆን፣ የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ የልጃገረድ ሴቶች ጥናት ለማደረግ መፈለጌን ለቤተሰቦቼ ስነግራቸው ተቀበሉኝ፡፡ ጥናቱን ከጀመርኩ በኋላ ብዙ ለዉጥ አይቼባቸዋለሁ፡፡ ጥናቱን ስናደርግ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ነገር አሳሳቢ ነበር፡፡ ህብረተሰቡ በአብዛኛው መረጃ አልነበረውም፡፡ መረጃ ለመስጠትም አንዳንዶች ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ ነገር ግን ያለዉን ሁኔታ በማስረዳት እንዲገነዘቡን አድርገናቸዋል፡፡ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ተቋሞችም መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አልነበሩም፣ አንዳንዶች ጥናቱን አጥንታችሁ ለውጥ አታመጡም የሚል ግንዛቤ ነበራቸው፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ እናንተ ልጆች ናችሁ የሚል ነው፡፡ ይሄን መነሻ በማድረግ የግንዛቤ ችግሮች እንዳሉ ተረድተን እኛም የቻልነውን ጥረት በማድረግ መረጃ ለማግኘት ሞክረናል፡፡ ከጥናቱ በኋላ ግን በህብረተሰቡ ላይ ብዙ ለውጦች አይተናል፡፡

ጥናቱን ካደረግን በኋላ በሴቶች ላይ የሚደረገውን ጥቃት ለመቀነስ ማህበረሰቡን ማስተማር፣በየትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሚኒ ሚድያዎች መልዕክት ማስተላለፍ፣ ለወጣት ሴቶች ትምህርትና ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በኔ ዕምንት ወጣቶች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ሪፖርት የሚያደርጉበትና ራሳቸውን ከጥቃት ለመጠበቅ የሚመቹ የወጣት ማዕከል በብዛት ቢኖሩ ብዙ ችግሮች ይቀረርፋሉ የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ላይ ዓይነተኛ የሚባሉ ለውጦች እንዲታዩ ብዙ ስራዎች ይቀራሉ፡፡ ስለዚህ እንደ ችግሩ ስፋት ብዙ ስራዎች መሰራት አለባቸው፡፡ እኛ ያደረግነዉ ጥናት የተወሰኑ ችግሮችን ቢቀርፍ ነው፡፡ የበኩላችንን አድርገናል ፤ ነገር ግን ብዙ መስራት እንዳለብን ይሰማኛል፡፡ እኔ ለውጥ አመጣለሁ ብዬ የማስበው በአካባቢያችን የሚገኙ ግንዛቤውና ዕውቀቱ የሌላቸውን በማስተማር ራሳቸውን ከችግሮቹ በፊት እንዲከላከሉ ፣ እንዲሁም ችግሮች ሲከሰቱ ለሚመከከታቸዉ አካላት ሪፖርት በማድረግ ችግሮቹ በሚቀረፉበት ዙሪያ አስተዋፅኦ ለማበርከት ጥረት አደርጋለሁ፡፡

ሻሎም መኮንን እባላለሁ፡፡ እድሜዬ 20 ነው፡፡ ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በማርኬቲንግ ትምህርት ዘርፍ ተመርቄያለሁ፡፡ ከጥናቱ በፊት የነበረኝ አመለካከት ለየት ያለ ነበር፡፡ የኔ ሚና  ጥናቱ የሚደረግበት ቦታ ሂጄ፣ የጥናቱን መረጃ ሰብስቤ በመምጣት ባቻ እንደሚያልቅ ነበር የማስበው፡፡ ነገር ግን ጥናቱን ሳደርግ ያየኋቸዉን ችግሮች ተረድቼ መፍትሄ መስጠትም እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡ የጥናቱ ዋናው ቁም ነገር  ለችግሮቹ መፍትሄ ማምጣት እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡

ቤተሰቦቼ ጥናቱን ሳካሂድ ያበረታቱኝ ነበር፡፡ በሴቶች ጥቃት ዙሪያ ግንዛቤም ነበራቸው፡፡ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ችግሮች አጋጥመውናል፡፡ ጥናቱን ለማድረግ በየቦታዉ ስንንቀሳቀስ የሚተናኮሉን ሰዎች ነበሩ፡፡ እንዲሁም ጥናት ለማድረግ በምንሄድበት ጊዜ አንዳንድ ተቋማት ፍቃደኛ አለመሆንና መረጃ ከመስጠት የመቆጠብ ችግሮች ነበሩ፡፡ ሰዎችን በትዕግስት በመቅረብና በማናገር፣ በማሳመን የምንፈልገውን መረጃ ለማግኘትጥ ጥረቶች አድርገናል፡፡ የጊዜ ቀጠሮ በመስጠትና በትዕግስት በማያዝ፣ መረጃውን እስክናገኝ ድረስ በመጠበቅ ያጋጠሙንን ችግሮች መቅረፍ ማየት ችለናል፡፡ ነገር ግን ችግሮቹ ሰፊ ስለሆኑ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረዉ እና የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ ብዙ ስራ እንደሚያስፈልግ ተረድቻለሁ፡፡ ወደፊት በህበረሰቡ ውስጥ ተፅዕኖዬን ማሳረፍ  እፈልጋለሁ፡፡ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ፣ ሴት ልጆችን ማስተማር እፈልጋለሁ፡፡

ማስተላለፍ የምፈልገው ነገር አለኝ ሰዎች ስለሴቶች ያለን አመለካከት መቀየር አለበት፡፡ ለሴቶችና ወንዶች የሚሰጠውን ስፍራ በሚመለከትም እንዲሁ፡፡ ስራን ለሴትና ለወንድ ብሎ መከፋፈል አስፈላጊ አይደለም፡፡ ሁለቱም ጾታዎች  እኩል እንደሆኑ ማህበረሰቡን ማስተማርና ለውጥ እንዲያመጣ ብዙ መሰራት አለበት ብዬ አስባለሁ፡፡




## ሻሎም መኮንን






## ፈሪሃ ሙሰማ

ስሜ ፈሪሃ ሙሰማ ይባላል፡፡ እድሜዬ 20 ሲሆን የ አይቲ ተማሪ ነኝ፡፡ ጥናቱን ከማድረጌ በፊት ብዙም ግንዛበቤ አልነበረኝም፡፡ ይሄን ጥናት ካደረግኩ በኋላ ግን ግንዛቤ ጨምሯል፡፡ ቤተሰቦቼ ስለጥናቱ ስነግራቸው ግንዛቤያቸው መጠነኛ እንደነበር ተረድቻለሁ፡፡በሂደት፣በየቀኑ የሰራነውን፣ዉሎአችንን ሳስረዳቸው ግን የበለጠ እየተረዱኝ መጡ በሂደቱ ላይ አንዳንድ  ጠቃሚ ሀሳቦችንና ምክሮችን ሰጥተውኛል፡፡
የማህበረሰቡ አባላት ወደ ጥናቱ ከመግባታችን  በፊት ምንም አይነት ግንዛቤ ያልነበራቸዉ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከጠበቅነው በላይ ስለ ጥናቱ ግንዛቤ የነበራቸውና የረዱን ሰዎችም እንዳሉ ነው፡፡ ጥናቱን ስናደርግ ችግሮች አጋጥመውናል፡፡ የምናናግራቸዉ ሰዎች ፍቃደኛ ባለመሆን ያመላልሱን ነበር፡፡ እንዲሁም በየመንገዱ የሚተናኮሱና የሚሳደቡ ሰዎችም ነበሩ፡፡የሚገጥሙንን ችግሮች ለመፍታት ከሱፐርቫይዘር እና ከአስተባባሪዎች ጋር በመሆን ስንሰራ ነበር፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ በመሆኔ  ደስተኛ ነኝ፡፡ ብዙ ነገር ተምሬበታለሁ፡፡

በሴቶች ላይ ለሚደርሰዉ ጥቃት ዝም ማለት እንደሌለብኝ ተምሬያለሁ፣ ማህበረሰቡ የባህሪ ለዉጥ ማምጣት አለበት ብዬ አስባለሁ፡፡ በህግ በኩል ክፍተት አለ ብዬ አስባለሁ፣ ምክንያቱም ጥቃት አድራሾች ተመጣጣኝ እና በቂ እርምጃ እየተወሰደባቸዉ አይደለም፡፡ ከግለሰብ ጀምሮ ሁሉም አካላት የራሳቸዉን ሀላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡ በተለይ የሴቶች ጥቃት እንደ ተራ ነገር እየተወሰደ ይገኛል፡፡ ሁላችንም በጋራ ተረባርበን  ችግሩን መቅረፍ አለብን እላለሁ፡፡

“ሸዋነሽ ሲሳይ እባላለሁ፡፡ 16 ዓመቴ ነው፡፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ አብዮት ቅርስ ትምህርት ቤት ነው የምማረው የምኖረው ከቤተሰቦቼ ጋ ነው ፡፡ ወደፊት ሞዴሊስት መሆን እፈልጋለሁ ገጣሚም መሆን እሻለሁ የልጃገረድ ጥናት ላይ በመሳተፌ ሞዴሊስት እና ገጣሚ ከሆንኩ በኋላ ለሴቶች ድምፅ በመሆን የእነሱ መፍትሄ መሆን እፈልጋለሁ ደግሞም እሆናለሁ!! ለራሴ፣ ለቤተሰቤ፣ ለጓደኛዬ ምሳሌ መሆን አፈልጋለሁ፡ ባለ ሙሉ ተስፋና ልበ ሙሉ ነኝ፡፡ ጥናቱ በህይወቴ ላይ ለውጥ እንዳመጣ አምናለሁ፡፡ ነገሮችን በሚገባ እንድረዳ፣ ሴት እህቶች ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶች መከላከል እንድችል እና ግንዛቤ እንዲኖረኝ አድርጎኛል፡፡ ሴት እህቶች ብዙ ችግሮች እንዳሉባቸው ተረድቻለሁ፡፡ ቀደም ሲል ቤተሰቦቼ ስለጉዳዩ ብዙ ግንዛቤ አልነበራቸዉም፡፡ እኔንም የተረዱኝ ጥናቱን ከጀመርኩ በኋላ ነዉ፡፡ እንደዚህ አይነት ችግሮች በማህበረሰቡ ውስጥ በስፋት መኖራቸውንም ብዙም አያወቁም ነበር፡፡ ጥናቱን አድርጌ ከመጣኍ በኋላ ያየኋቸውን ችግሮች ስነግራቸው ደግሞ በበለጠ ሊረዱኝ ችለዋል፡፡ በጥናቱ ወቅት ማህበረሰቡ ለሴት ልጆች ዝቅተኛ አመለካከት እንዳለው አይተናል፡፡ ለኛም የነበረው አመለካከት የተዛነፈ ነበር፡፡ እናንተ ልጆች ናችሁ ያሉንም ነበሩ፡፡ አንዳንዶችም ጥናቱ ውጤት ያመጣል ብለው አያስቡም ነበር ጥናቱን ስንጀምር መንገድ ላይ አንዳንድ ልጆች ይተናኮሉን ነበር፡፡ አንዳንዶች ብር እንድንሰጣቸው ይጠይቁን ነበር፡፡ ነገር ግን በተሰጠን ስልጠና መሰረት የገጠሙንን ችግሮች ተሸግረን ጥናቱን ማካሄድ ችለናል፡፡ ከጥናቱ ያገኘሁት ውጤት ከሌሎች ሴቶች ወጣቶች በበለጠ እራሴን በሚገባ እንድረዳ አድርጎኛል በራስ መተማመኔን ከፍ አድርጎታል፡፡ የሌሎችን ወጣት ሴቶች ችግርም እንድረዳ አድርጎኛል፡፡ የማህበረሰብ ለውጥ ጥናቱን በምናደርግበት ወቅት ተሳታፊዎቹ ስለሴቶች ጥቃት እና መከላከያ መንገዶች ከእኛ ያገኙት ግንዛቤ ነበረ፡፡ በተመሳሳይ እኛም ከማህበረሰቡ ብዙ ነገሮችን የተማርንበትን ዕድል ፈጥሮልናል፡፡ ሴት ልጆች ግንዛቤ በመስጠትና በማስተማር በራሳቸው እንዲተማመኑ የበኩሌን ድርሻ መወጣት እፈልጋለሁ፡፡ በቤታቸው በብዙ ችግሮች ዉስጥ ያሉ እና ጥቃት የደረሰባቸዉን ሴቶች ማገዝ መርዳት እንዳለብን አስባለሁ ዝም መባል የለበትም አመሰግናለሁ፡፡”




# ሸዋነሽ ሲሳይ




# ፍቅር ፀሃይ

"

ስሜ ፍቅር ፀሃይ ይባላል፡፡ 17 ዓመቴ ነው፡፡ አዲስ አባባ አጎና ሲኒማ አካባቢ መንደራችን ሲሆን የምኖረዉ ከእናቴና ወንድሜ ጋር ነው፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ የምማረው ፍሬህይወት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ለወደፊት ዶክተር የመሆን እቅድ አለኝ፡፡ እንዲሁም በሀገራችን ያለውን በሴቶች ላይ በሚንፀባረቁ አመለካከቶች ዙሪያ ጥናቶችን ማካሄድ እፈልጋለሁ፡፡

"

“ከጥናቶቼ ባገኘኋቸው ግኝቶች መነሻ አሉታዊ አመለካከቶችን ወደ አዎንታዊነት ለመቀየርጥረት አደርጋለሁ የወደፊት ራዕዬ ይህ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ጥናት ተሳታፊ በመሆኔ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ዕድለኛ እንደሆንኩም አስባለሁ፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ተሳታፊ መሆኔ ለሴት ልጅ አሁንም የሚጨነቅላት አካል አለ ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል፡፡ እራሴን እንዳበቃም ረድቶኛል፡፡ ለሴት ልጅና ለራሴ ያለኝን አመለካከት እንድቀይር ረድቶኛል፡፡”




# ፀጋነሽ ሀይሉ

“ፀጋነሽ ሀይሉ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ 19 ነው፡፡ለየት ያለ ባህሪ አለን ብዬ አስባለሁ ለሚገጥሙኝ ችግሮች እጅ አልሰጥም፡፡ ከጥናቱ በፊት በማህበረሰባችን ውስጥ  የሴቶች ጥቃት በብዛት ስለመኖሩን መረጃዎች አልነበሩኝም፡፡ ነገር ግን ጥናቱን ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ የተለዩ ስሜቶችን አስተናግጃለሁ፡፡ የሰዎችን ደስታ ሳይ ደስ ይለኛል፡፡  ችግሮቻቸውን ሳይና ስሰማም ስሜቴ ይነካል፡፡ ስሜቶቻቸውን ለመረዳት እጥራለሁ፡፡ ከዚህ በፊት በራስ መተማመን ብቃት የለኝም ነበር፡፡ በሰዎች ፊት ቆሜ ብዙ የማውራት ልምድ አልነበረኝም፡፡ ነገር ግን በአክሽንኤይድ ኢትዮጵያ አማካኝነት ስልጠና ወስጄ ይሄንን ጥናት ካደረግኩ በኋላ ግን በራሴ ላይ ብዙ ለውጦች አይቻለሁ፡፡

ወደፊት መስራት እምፈልጋቸው ነገሮች አሉኝ፡፡  ሴቶችን ማስተማርና ችግሮቻቸውን  አሸንፈው ለዉጥ እንዲያመጡ መርዳት እፈልጋለሁ፡፡ የልጃገረድ ሴቶች ጥናት ከማድረጋችን በፊትም ቢሆን ቤተሰቦቼ ስለ ሴቶች ጥቃት ግንዛቤ ነበራቸው፡፡ ሀሳቦችን እንለዋወጣለን ፤ ከእህቴ ጋር እናወራለን፡፡ ጥናት የምናደርግበት አካባቢ ማህበረሰብ በተወሰነ መልኩ ግንዛቤ ነበረው፡ ነገር ግን ከችግሩ ስፋት አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል እንደ ችግር ያየነዉ  ወጣቶች ስለ ጉዳዩ ብዙ እንዲነሳ እና እንዲወራ ፍላጎት አልነበራቸውም ፡፡ ይህም የሚያሳየው የግንዛቤ እጥረት እና የአመለካከት ችግሮች መኖራቸውን ነው፡፡

ከወጣቶች ፣ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ተቋማትን ስለምንሰራዉ ስራ ግንዛቤ አስጨብጠን፣ የአንዳንዶቹን ልምድ ሰምተን የልምዶቻቸውን መረጃዎች  መሰብሰብ ችለናል፡፡ የአመለካከት ችግሮች የነበሩባቸውንም ለውጥ እንዲያመጡና ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ግንዛቤ ሰጥተናል፡፡ እኔ ለወደፊት ሴቶችን ማስተማር፣ በራስ መማመን አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ ፣ በችግሮቹ ዙሪያ እንዲወያዩ እና መፍትሄ እንዲያመጡ ፣ እድሎችና አማራጭ መንገዶችን እንዲያገኙ በማድረግ እችላለሁ ብለው እንዲነሱና እንዲለወጡ የበኩሌን አስተዋፅኦ ማበርከት እፈልጋለሁ፡፡”





ኤፍራታ ተስፋዬ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ 18 ሲሆን የተወለድኩት አርሲ ነው፡፡ ስድስት አመት ሲሆነኝ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ትምህርት ጀመርኩ፡፡ ከ 1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 መተባበር የመጀመርያ ትምህርት ቤት ተምሬ አጠናቅቄያለሁ፡፡ ከሰዎች ጋር ብዙ መግባባት ባልችልም ጎበዝና ጠንካራ ተማሪ ነኝ፡፡ 8ኛን ክፍል እንደጨረስኩ በክረምት ወቅት በወወክማ ኢትዩጵያ ድርጅት በቋንቋ፣ቢዝነስ፣ሊደርሽፕ፣ምግብ ዝግጅት እና ሌሎች የህይወት ክህሎት ስልጠናዎች በማግኘቴ በራስ የመተማመን ብቃቴን ጨምሯል፡፡ የ10ኛ ክፍል ትምህርት ስጨርስ በወወክማ በምግብ ሙያ ለ3 ወር ስልጠና ወሰድኩኝ ምግብ ሙያ ስራ ደስ የሚለኝ የሙያ ዘርፍ ነዉ፡፡

# ኤፍራታ ተስፋዬ



ስልጠና ካጠናቀቅኩ በኋላ በአክሽን ኤይድ ኢትዩጵያ የሚሰራ የልጃገረድ ሴቶች ጥናት ላይ እንድሳተፍ እድሉን አግኝቼ ጥናቱን አደረግኩ፡፡ ጥናቱ በህይወቴ ላይ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ከጥናቱ በፊት የቤተሰቤ አመለካከት የተስተካካለ አልነበረም፡፡ የጥናቱን ውጤት ካዩ በኋላ ግን አመለካከታቸዉ ብዙ ተለውጧል፡፡ የማህበረሰቡን ምላሽ በተመለከተ፣ በጥናቱ ወቅት አንዳንዶቹ ስራችንን በተገቢዉ መልኩ የምንወጣ አልመሰላቸውም ነበር፡፡

የአመለካከት ችግሮች ነበሩ፡፡ ለጥናቱ መረጃዎች ፍለጋ ወደቤታቸው ስንሄድ በራቸዉን የሚዘጉም ነበሩ፡፡ በኋላ ላይ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የችግሩን አሳሳቢነት ስናስረዳቸዉ ብዙ ለውጦች መጥተዋል፡፡ ለመጀሪያ ጊዜ ነበር ጥናቱን ያካሄድነው፡፡ በዚህም ችግሮች ነበሩ፡፡ የእግር ጉዞው አድካሚ ነበረ፡፡ ጥናቱን በምናደርግበት ጊዜ የሚተናኮሉን ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን እነዚህን ችግሮች ተቋቁመን ጥናቱን ዳር ማድረስ ችለናል፡፡

ከጥናቱ በኋላ እራሴን በደንብ እንዳይ አስችሎኛል፣ ነገሮችን በጥልቀት እንድመለከትና ጠንካራ ሴት እንድሆን እና የሚመጡ ማናቸዉንም ጫናዎች ተቋቁሜ ብዙ ነገሮችን ሰርቼ ማሳካት እንደምችል ተምሬያለሁ፡፡ ከጥናቱ በፊት ብዙ ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡

እኛ ግን የምናውቃቸውን የተለያዩ ታሪኮች ስናካፍላቸው ከራሳቸው ህይወት ጋር በማገናኘት ታሪካቸውን ያካፈሉን ሰዎች ነበሩ፡፡በሴቶች ላይ ብዙ ማህበራዊ ችግሮች እንዳሉ ተረድቻለሁ፡፡ በነዚህ ችግሮች ዙሪያ ሰርቼ ለውጥ ማምጣትና ለብዙ ሴቶች ምሳሌ መሆን እፈልጋለሁ፡፡



## ነፃነት ዳንኤል

"ነፃነት ዳንኤል እባላለሁ፡፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ የምማረው አብዮት ቅርስ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ከእናቴ፣ እህቴና ከወንድሜ ጋር ነው የምኖረው፡፡ የዚህ ጥናት ተሳታፊ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፡፡ በአክሽን ኤይድ ኢትዩጵያ እና ወወክማ ትብብር ህፃናት ሴቶች ላይ ጥናት በመስራታችን ብዙ ለውጥ እናመጣለን ብዬ አስባለሁ፡፡

የጥናቱን ግኝቶች መነሻ አድርጌም ወንዶች ወይም የጥቃቱ አድራሾችን ግንዛቤ በማስጨበጥ በህፃናትና ሴቶችች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እንቀንስ እላለሁ፡፡ ትምህርት ቤቴ ውስጥ አንዷት ጓደኛ አለችኝ፡፡ በሴቶች ጥቃት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን እያነሳች ሌሎች ጓደኞቻችንን ትመክራለች፡፡ እኔንም ፡፡ ወጣት ሴቶች ፆታዊ ጥቃቶችን እንዴት መከላከል ይችላሉ፣ ጥቃት ከደረሰባቸው በኋላስ ምን ማድረግ አለባቸው ? በሚሉ ጉዳዩች ዙሪያ እንመካከራለን፡፡ እናቴን በጣም ነው የምወዳት፡፡ በብዙ ነገሮች ታግዘኛለች፡፡ እንደ ጓደኛ ነው የምናወራው ፡፡ ትመክረኛለች፡፡ ነገሮችን በግልፅ ነው የምናወራው፡፡ ደስተኛ ነኝ፡፡"






## ቤተልሄም መሃመድ

"ቤተልሄም መሃመድ እባላለሁ፡፡ የተወለድኩት አዲስ አበባ ዕድሜዬ 15 ነው፡፡ የምማረው አብዮት ቅርስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ የ9ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ከቤተሰቦቼ ጋር ነው የምኖረው፡፡ 1 ወንድምና 3 እህቶች አሉኝ፡፡ የምታሳድገን እናቴ ናት፡፡ ቀደም ሲል ኑሯችን ዝቅተኛ ነበር፡፡ እናቴ ታታሪና ጠንካራ ሴት በመሆኗ ግን አሁን ላይ ኑሯችን ከቀድሞው የተሻለ ሆኗል፡፡ ጥናቱ ብዙ ነገሮችን አስተምሮኛል፡፡ ሴቶች ላይ የሚደርሱትን ጫናዎች ተረድቼያለሁ፡፡ ጫናዎቹንና እና ችግሮቹን እንዴት መፍታት እንደምችል አውቄያለሁ፡፡

ከጥናቱ በፊት ስለኔ ተሳትፎ ቤተሰቤ በቂ ግንዛቤ አልነበረውም፡፡ ከቤት ርቄ አላውቅም፡፡ ጥናቱ ደግሞ ራቅ ማለትን ይጠይቅ ነበር፡፡ ለተወሰኑ ቀናት ስልጠና እና ገለፃ ተደረገልን፡፡ ከስልጠናውና ከገለፃው በኋላ ቤተሰቦቼም ሀሳቡን እና በሴቶች ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶች ተረዱ፡፡ ከዚህ በኋላ አብረውኝ ከተመደቡ ጓደኞቼ ጋር አብረን ጥናቱን ጀመርን፡፡ ጥናቱን ስናደርግ ለቤተሰቦቻችን ያየናቸውን ችግሮች እንነግራቸዉ ነበረ እነሱም አንዳንድ ምክረ ሀሳቦች ይሰጡን ነበረ፡፡
ህብረተሰቡ በጥናቱ ዙሪያ ብዙ እውቀት አልነበረውም፡፡ በኋላ ግን ማህበረሰቡን ለማሳመን ጥረት አድርገናል:: በዚሁ መሰረት የጥናቱን አስፈላጊነት በማስረዳት አስፈላጊዉን መረጃ እንዲሰጡን አድርገናል፡፡

በአጠቃላይ ሴቶች ላይ ያለውን ጫና እንዴት መቀነስ እንዳለብን እና የሚደርስባቸዉን ጥቃት እንዴት መከላከል እንዳለብን ተምሬያለሁ፡፡ ለወደፊት እኔ ሴቶችን ለመርዳት እና ለማስተማር የቻልኩትን ሁሉ አደርጋለሁ የሚል እቅድ አለኝ፡፡"










YMCA ETHIOPIA

actionaid



actionaid

ጥናቱን ያደረጉት ልጃገረድ ሴቶች ከጥናቱ በኋላ ያገኙትን ትምህርትና ልምድ ሲያካፍሉ



Supported by players of PEOPLE'S POSTCODE LOTTERY

Awarded funds from POSTCODE INTERNATIONAL TRUST

## ወወክማ

ቂርቆስ ክ/ከ፣ ወረዳ 3
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

+251_114_701_035

admin@ymcaethiopia.org
34340
www.ethioymca.org

## አክሽንኤይድ ኢትዮጵያ

**ለሚኩራ ክፍለ ከተማ፣**
**ቀበሌ 13፣ የቤት ቁጥር 3044**

**1261, አዲስአበባ , ኢትዮጵያ**

ethiopia.actionaid.org
@ActionAidE
@ActionAid Ethiopia
Comms.Ethiopia@actionaid.org